# መጽሐፈ መሳፍንት

ይህ መጽሐፍ እስራኤላውያን ወደ ከነአን ምድር ገብተውና ተዋግተው ከወረሱአትና ኢያሱ ከሞተ በኋላ ይተዳደሩበት የነበረውን የመሳፍንት ዘመን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ይህ ዘመን ከኢያሱ ሞት ጀምሮ በሳሙኤል አማካይነት ንጉሥ ሳዖል እስከ ነገሠበት ዘመን ድረስ ያለውን ጊዜ ያጠቃልላል፡፡ 1ነገ. 6፡1 እና ሌሎች ክፍሎችን ስናገናዝብ፤ ከግብጽ ከወጡ ጀምሮ እስከ ሰሎሞን አራተኛ ዓመት ድረስ 480 ዓመታት ከሆነ፤ 40 ዓመት የምድረ በዳ መቅበዝበዝ፣ 40 ዓመት የሳዖል ንግስና፣ 40 ዓመት የዳዊት ንግሥና፣ እንዲሁም እስከ ሰሎሞን አራተኛ ዓመት ድረስ በአጠቃላይ 124 ዓመታት ሲቀነስ፤ 480-124= 356 ዓመታት ይቀራል፡፡ በመጽሐፈ ኢያሱ እንዳየነው ኢያሱ በተስፋይቱ ምድር ወደ 25 ዓመታት ኖረ ብንል፤ 356-25= 331 ይሆናል፡፡ የመሳፍንት ዘመን ወደ 330 ዓመታት ያህል ይሆናል ማለት ነው፡፡

| | | |
|---|---|---|
| 1 | ከአብርሃም መወለድ እስከ ዮሴፍ ሞት | ወደ 400 ዓመታት |
| 2 | ከዮሴፍ ሞት ከግብጽ ባርነት እስከ መውጣት | ወደ 400 ዓመታት |
| 3 | ከግብጽ ባርነት መውጣት እስከ ንጉሥ ሳዖል መንገሥ | ወደ 400 ዓመታት |
| 4 | ከንጉሥ ሳዖል እስከ ንጉሥ ሴዴቅያስ (የመጨረሻው የይሁዳ ንጉስ) በባቢሎን መማረክ | ወደ 400 ዓመታት |
| 5 | ከባቢሎን ምርኮ እስከ መሲሁ | ወደ 400 ዓመታት |

በዚህ መጽሐፍ፤ በመሳፍንት ዘመን ከተደረጉት ድርጊቶች ውስጥ ታሪካዊ የሆኑት ነገሮችና የ12 መሳፍንት ስሞች ተጠቅሰዋል፡፡ ከ12ቱ መሳፍንት ውስጥ 6ቱ ብቻ ጠለቅ ባለ መልክ ጎልተው ሲታዩ ሌሎቹ ግን በአጭሩ እንደተጠቀሱ እናያለን፡፡

ይህ ዘመን እግዚአብሔር ራሱ በእስራኤል ላይ ንጉሥ የነበረበት ዘመን ነበረ፡፡

ይህንን መጽሐፍ ማን እንደጻፈው በግልጽ ባይታወቅም ነቢዩ ሳሙኤል እንደጻፈው ይታመናል:: ይህ ነቢይ በመሳፍንት ዘመንና በነገሥታት ዘመን መካከል የነበረ፤ የመጀመሪያ የእስራኤል ንጉሥ የነበረውን ሳዖልን የቀባ እንደመሆኑ መጠን የመሳፍንትን ዘመን ታሪክ በደንብ አድርጎ የሚያውቅ ስለነበረ የእርሱ ጸሐፊነት በብዙ አካባቢ ተቀባይነት አለው::

በዚህ መጽሐፍ የምናነባቸው ታሪኮች በጣም የሚያሳዝኑ፣ በመጽሐፈ ኢያሱ ውስጥ ያየነውን የድል ታሪክ ተቃራኒ የሆኑ፤ የሽንፈት፣ የጭንቀትና የጉስቁልና ታሪኮች ናቸው:: ይህም የሆነበት ምክንያት ኢያሱና፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል ያደረገውን የሚያውቁ ሽማግሌዎች ሁሉ ከሞቱ በኋላ እስራኤል ከእግዚአብሔር ርቆ ባዕድ አምልኮን ስለጀመረ ነበር (መሳ. 2:7)::

የዚህ መጽሐፍ ዋና መልእክት፣ <u>ከኃጢአትና ከጠላት ጋር መደራደር (Compromise) የሚያመጣውን ውድቀት የሚያሳይ ነው::</u> ጠላት ካላጠፋነው እንደሚያጠፋን: ኃጢአትን ካባበልነው እንደሚገድለን በጉልህ የሚያሳይ መጽሐፉ ነው::

<u>የመጽሐፉ አከፋፈል</u>

I. የመጽሐፉ መግቢያ የሆኑ ሐሳቦች (ምዕ 1-2)
II. የመሳፍንቶች ታሪክ (ምዕ 3- 16)
III. አንዳንድ ታሪካዊ ድርጊቶች (ምዕ 17- 21)

## I. የመጽሐፉ መግቢያ (ምዕ 1- 2)

መሳፍንት ምዕ. 1:- በኢያሱ ዘመን የነበሩ የእግዚአብሔርን ሥራ የሚያውቁ ሰዎች በነበሩት ጊዜ ስለተደረጉ አንዳንድ የድል ታሪኮች ይናገራል:: ከይሁዳ ነገድ የሆነውን የካሌብንም ታሪክ በአጭሩ ይጠቅሳል::

መሳፍንት ምዕ. 2:- የአጠቃላይ የመጽሐፈ መሳፍንትን ሐሳብ ያጠቃለለ ምዕራፍ ነው::

እስራኤላውያን እንዴት የእግዚአብሔርን ቃልኪዳን ተላልፈው ባዕድ አማልክትን እንዳመለኩ፤ የእግዚአብሔርም ቁጣ በእነርሱ ላይ እንደነደደና አሳልፎ ለጠላቶቻቸው እንደሰጣቸው፤ በጭንቀታቸው ጊዜ እንዴት ወደ እግዚአብሔር እንደጮኹ፤ እግዚአብሔርም ጩኸታቸውን ሰምቶ የሚታደጋቸውን መስፍን እንዳስነሳላቸው፤ መስፍኑ በሕይወት ባለበት ዘመን እግዚአብሔርን እንዳመለኩ፤ መስፍኑ ከሞተ በኋላ ግን እንደገና ባዕድ አምልኮ እንደ ጀመሩና በጠላት እጅ እንደወደቁ ተደጋጋሚ የሆነ ታሪክ መሆኑን ያስረዳል።

## II. <u>የመሳፍንቶች ታሪክ</u> (ምዕ 3- 16)

በዚህ ክፍል 12 መሳፍንት ተጠቅሰዋል፡

| ተ.ቁ. | ስም | የገዛበት ዘመን | ምዕራፎች |
|---|---|---|---|
| 1. | ጐቶንያል (የካሌብ ታናሽ ወንድም ልጅ) | 40 ዓመታት | (ምዕ 3፡9-11) |
| 2. | ናዖድ | 80 ዓመታት | (ምዕ 3፡15-30) |
| 3. | ሰሜጋር | አልተጠቀሰም | (ምዕ 3፡31) |
| 4. | ዲቦራና ባርቅ (በአንድነት) | 40 ዓመታት | (ምዕ 4፡4-5፡31) |
| 5. | ጌድዮን | 40 ዓመታት | (ምዕ 6፡11-8፡35) |
| 6. | ቶላ | 23 ዓመታት | (ምዕ 10፡1-2) |
| 7. | ኢያዕር | 22 ዓመታት | (ምዕ 10፡ 3-5) |
| 8. | ዮፍታሔ | 6 ዓመታት | (ምዕ 11፡1-12፡7) |
| 9. | ኢብጻን | 7 ዓመታት | (ምዕ 12፡ 8-10) |
| 10. | ኤሎም | 10 ዓመታት | (ምዕ 12፡ 11-12/ |
| 11. | አብዶን | 8 ዓመታት | (ምዕ 12፡ 13-15/ |
| 12. | ሳምሶን | 20 ዓመታት | (ምዕ 13፡2 ምዕ.16፡31/ |

ከእነዚህ 12 መሳፍንት ውስጥ 6ቱን ብቻ ሰፋ ባለ መልክ ተጠቅሰው እናያለን እነዚህ 6 መሳፍንት ከእስራኤላውያን 6 ጊዜ በባዕድ አምልኮ መውደቅና 6 ጊዜ ወደ እግዚአብሔር መጮህ ጋር አብረው የሚሄዱ እንደሆነ ከሚቀጥለው ሠንጠረዥ እንረዳለን፡፡

| ተ.ቁ | የእስራኤል ክህደት | በጠላት መሸነፍ | የተገዙበት ዘመን | ከጠላት ያዳናቸው መስፍን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ምዕ. 3፡5-8 | በመስጴጦምያ ንጉሥ በኩሰርሰቴም | ለ8 ዓመታት | ጎቶንያል |
| 2. | ምዕ. 3፡12-14 | በሞአብ ንጉሥ ዔግሎም | ለ18 ዓመታት | ናዖድ |
| 3 | ምዕ. 4፡1-3 | በከነዓን ንጉሥ ኢያቢስ | ለ20 ዓመታት | ዲቦራና ባርቅ |
| 4 | ምዕ. 6፡1-10 | በምድያማውያን | ለ7 ዓመታት | ጌድዮን |
| 5 | ምዕ. 10፡6-18 | በፍልስጥኤማውያን (የአሞን ልጆች) | ለ18 ዓመታት | ዮፍታሔ |
| 6 | ምዕ. 13፡1 | በፍልስጥኤማውያን | ለ40 ዓመታት | ሳምሶን |

በእነዚህ 6 ተመሳሳይ ታሪኮች ውስጥ 4 ነገሮችን በተደጋጋሚ እናያለን፡

ሀ) ኃጢአት (ባዕድ አምልኮ)

ለ) መከራ (በጠላት መጠቃት)

ሐ) እግዚአብሔርን መማጸን

መ) የእግዚአብሔር ማዳን




<u>ኃጢአትና መከራ:-</u> ምንጊዜም የማይነጣጠሉ ናቸው::

«ኃጢአትን የሚዘራ መከራን ያጭዳል» ምሳሌ 22:8

እንዲሁም:

<u>እግዚአብሔርን መማጸንና የእግዚአብሔር ማዳን</u> የማይነጣጠሉ ናቸው::

«በመከራ ቀን ጥራኝ (ተማጸነኝ) አድንህማለሁ አንተም ታከብረኛለህ» መዝ 50:15

ከዚህ መጽሐፍ የምንማረው ዋና ትምህርት ከጠላታችን ጋር ሊኖረን የሚገባውን ግንኙነት ነው:: እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን አክብረው በሚመላለሱበት ጊዜ ጠላቶቻቸው ከእግራቸው

በታች ሆነው እናያለን፤ የእግዚአብሔርን ቃል ኪዳን በሚተላለፉበት ጊዜ ግን ጠላቶቻቸው በእነርሱ ላይ ሲሰለጥኑና ሲቀጠቅጧቸው እናያለን።

መሳ. ምዕ. 3:- የእስራኤላውያንን ከኃጢአትና ከጠላት ጋር መደራደር /Compromise/ ስናይ ቀስ በቀስ እንደነበረ ያሳየናል። እንዲሁም፤ ስለ ጐቶንያልና ስለ ናዖድ ድርጊት ይናገራል።

ምዕ 3፡5-6

በመጀመሪያ:- በጠላቶቻቸው መካከል <u>ተቀመጡ</u>
በሁለተኛ ደረጃ:- ከጠላቶቻቸው ጋር <u>ተጋቡ</u>
በሦስተኛ ደረጃ:- አማልክቶቻቸውን <u>አመለኩ</u>

ችግሩ በመጀመሪያ የመጣው በመካከላቸው ሲቀመጡ ነው።

የእግዚአብሔር ቃል እኛንም ያስጠነቅቀናል፡ «ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ ... በዋዘኞች ወንበር ያልተቀመጠ» መዝ. 1÷1

«ስለዚህም ጌታ፡ - ከመካከላቸው ውጡና የተለያችሁ ሁኑ፣ ርኩስንም አትንኩ፣ ይላል፤ ሁሉንም የሚገዛ ጌታ:- እኔም እቀበላችኋለሁ፣ ለእናንተም አባት እሆናለሁ እናንተም ለእኔ ወንድ ልጆችና ሴት ልጆች ትሆናላችሁ ይላል፤» 2ቆሮ 6፡17-18።

ምዕ. 4:- ስለ ዲቦራና ባርቅ ድል መንሳት ይናገራል።

ነቢይቱ ዲቦራ በእስራኤል ላይ ትፈርድ እንደነበር፤ ባርቅንም «እግዚአብሔር... በእጅህ አሳልፌ እሰጠዋለሁ ብሎ አላዘዘህምን?» በማለት ወደ ጦርነት እንዲወጣ ስታበረታታው እናያለን። ለእህቶች ትልቅ ምሳሌና ማበረታቻ የምትሆን ትልቅ የእግዚአብሔር ሴት እንደሆነች እናነባለን። ወደ ጦርነት እንዲወጣ እግዚአብሔር አዝዞት የነበረው ባርቅ እንዲህ ብሎ ይመልስላታል «አንቺ ከእኔ ጋር ብትሄጂ እኔ እሄዳለሁ አንቺ ግን ከእኔ ጋር ባትሄጂ እኔ አልሄድም» /ቁ 8/ ።

ምዕ 5:- ዲቦራና ባርቅ የዘመሩት የድል መዝሙር።

ቁ. 7 «አንቺ ዲቦራ እስክትነሺ ድረስ ለእስራኤልም እናት ሆነሽ እስክትነሺ ድረስ ኃያላን በእስራኤል ዘንድ አነሱ አለቁም።» እያንዳንዳችን እግዚአብሔር ለጠራን ነገር እሺ ብለን እስከምንነሳ ድረስ ሳይሠራ ተወዝፎ የሚቀር ሥራ አለ። ያ ሥራ አለመሠራቱ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይጎዳል።

ቁ. 12 «....ባርቅ ሆይ ተነሣ፤ የአቢኒኤም ልጅ ሆይ ምርኮህን ማርክ» እያንዳንዳችን ተነሥተን መማረክ ያለብን በስማችን የተመደበልን ምርኮ (ድርሻ) አለን። እኛ ተነሥተን እስካልማረክነው ድረስ እንዲሁ ይቀራል። የስንቶቻችን ምርኮ ቆሞ እየጠበቀን ይሆን?

ቁ 23 «የእግዚአብሔር መልአክ፤ ሜሮዝን እርገሙ፤ እግዚአብሔርን በኃያላን መካከል ለመርዳት፣ እግዚአብሔርን ለመርዳት አልመጡምና የተቀመጡበትን ሰዎች ፈጽማችሁ እርገሙ አለ።»

ከዚህ ቁጥር እንደምንረዳው እግዚአብሔር በውጊያ ላይ እያለ እኛ እጃችንን አጣምረን ቁጭ የምንል ከሆነ (እግዚአብሔርን ለመርዳት የማንወጣ ከሆነ) እርግማንን በራሳችን ላይ እናመጣለን።

## የጌድዮን ታሪክ (መሳፍንት 6-8)

«የእስራኤልም ልጆች በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሠሩ፤ እግዚአብሔር በምድያም እጅ ሰባት አመት አሳልፎ ሰጣቸው። ከምድያምም የተነሳ የእስራኤል ልጆች በተራራ ላይ ጉድጓድና ዋሻ ምሽግም አበጁ።» በድል አድራጊነትና በነጻነት የጠላቶቹን ደጅ ወርሶ ዘፍ. 22፡17 መኖር የነበረበት የእግዚአብሔር ሕዝብ በኃጢአቱና በመተላለፉ ምክንያት ጠላት የእርሱን ደጅ ወርሶበት እንደ ሽኮኮና ቆቅ በጉድጓድና በዋሻ ውስጥ ተደብቆ (ተሸሽጎ) ሲኖር ምንኛ ያሳዝናል። (የነህምያን ጸሎት ተመልከት ነህ. 9፡36-37)። እኛስ በክርስቶስ ኢየሱስ ከአሸናፊዎች በላይ ሆነን በጠላት ኃይል ሁሉ ላይ ሠልጥነን (ሮሜ 8፡37፤ ሉቃ. 10፡19) መኖር ሲገባን

ከጠላት እየተሸሸግን ጠላት በእኛ ላይ ሠልጥኖብን እየተጠቃን የምንኖር ስንት ክርስቲያኖች አለን?

ምዕ. 6፡6 «ከምድያምም የተነሳ እስራኤል እጅግ ተጠቁ፡ የእስራኤልም ልጆች ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፡፡» በእንደዚህ ዓይነት ጥቃት ውስጥ ስንገኝ ያለን አማራጭ በንሥሐ ወደ እግዚአብሔር መጮህ ነው፡፡

እግዚአብሔር ጩኸታቸውን ሰምቶ ጌድዮንን ሲያስነሳላቸው እናያለን፡፡ የጌድዮን ታሪክ ለእያንዳንዳችን ትልቅ ትምህርት ያለው ታሪክ ነው፡፡ እግዚአብሔር ጌድዮንን ከጅምሩ እንዴት ይመለከተው እንደነበረና ጌድዮን ደግሞ ራሱን እንዴት ይመለከት እንደነበረ እንመልከት፤

ምዕ. 6፡12 «የእግዚአብሔርም መልአክ ለእርሱ ተገልጦ አንተ ጽኑዕ ኃያል ሰው እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው አለው፡» ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር ጌድዮንን እንዴት ይመለከተው እንደነበረ ያሳየናል፡፡ «አንተ ጽኑዕ ኃያል ሰው»፡፡

ጌድዮን ግን ራሱን ያይ የነበረበት አመለካከት በጣም ዝቅ ያለና ደካማ አመለካከት ነበር፡፡

ምዕ 6፡15 «እርሱም፡ ጌታ ሆይ እስራኤልን በምን አድናለሁ? ወገኔ ከምናሴ ነገድ ከሁሉ ይልቅ የተጠቃ ነው እኔም በአባቴ ቤት የሁሉ ታናሽ ነኝ አለው፡፡»

እነዚህ ሁለት አመለካከቶች በጣም የተራራቁ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡

እግዚአብሔር በጌድዮን ሕይወት ያለውን ዓላማ ለመፈጸም በመጀመሪያ የጌድዮንን አመለካከት ቀና ማድረግ ነበረበት፡፡ ጌድዮን ራሱን እግዚአብሔር እንደሚመለከተው ማየት ካልቻለ የእግዚአብሔርን ዓላማ መፈጸም አይችልም፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር በጌድዮን በኩል ከመስራቱ በፊት በጌድዮን ውስጥ መስራት ነበረበት፡፡

የተለያዩ የማበረታቻ ቃላቶችንና ድርጊቶችን በማከናወን ጌድዮን ራሱን እግዚአብሔር እንደሚያየው እንዲያይ ሲያደርገው እናያለን፡፡

በምዕ.7፡17-18 ላይ ጌድዮን ሕዝቡን እንዲህ ይላቸዋል፡

«እርሱም እኔን ተመልከቱ እንዲሁም አድርጉ እኔ እንደማደርግ እንዲሁ አድርጉ ቀንደ መለከታችሁን ንፉ <u>ለእግዚአብሔርና ለጌድዮን</u> በሉ አላቸው፡፡» ለእግዚአብሔርና ለጌድዮን በሉ፤ ማለቱ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔርና ጌድዮን ሙሉ በሙሉ በሐሳብ እንደተስማሙ ያሳየናል፡፡ እኛና እግዚአብሔር በሐሳብ ሙሉ በሙሉ ሳንስማማ እግዚአብሔር ዓላማውን በእኛ መፈጸም አይችልም፡፡

በምዕ 8:- የጌድዮንን የጦርነት ስልት ብቻ ሳይሆን የአስተዳደር ስልትም እናያለን፡፡

«የኤፍሬም ሰዎች ይህ ያደረግህብን ምንድር ነው ምድያምን ለመዋጋት በወጣህ ጊዜ ለምን አልጠራኸንም? አሉት <u>ጽኑ ጥልም</u> ተጣሉት፤ እርሱም እኔ ካደረግሁት እናንተ ያደረጋችሁት አይበልጥምን? የኤፍሬም ወይን ቃርሚያ ከአቢኤዝር ወይን መከር አይሻልምን? እግዚአብሔር የምድያምን መኳንንት ሔሬብንና ዜብን በእጃችሁ አሳልፎ ሰጥቶአቸዋል እናንተ ያደረጋችሁትን የሚመስል እኔ ምን ማድረግ እችል ኖሮአል? አላቸው፤ <u>ይህን በተናገረ ጊዜ ቁጣቸው በረደ</u>፡፡» «የለዘበች መልስ ቁጣን ታበርዳለች» (ምሳ. 15፡1) ተብሎ እንደ ተጻፈ፡፡

ምድያማዊያንን ከመውጋት ይልቅ ይሄ ከወገኖች የሚመጣው ውጊያና ጥል የበለጠ ጉዳት ሊያመጣ የሚችልና የእግዚአብሔርን ሐሳብ ሊያስተጓጉል የሚችል የጠላት አሠራር ነው፡፡ የእግዚአብሔር ሰው የሆነ መሪ ግን ለምን ተገፋሁ፣ ለምን ተጠየቅሁ ሳይል በትሕትና ራሱን ዝቅ በማድረግ የወገኖችን ቁጣ የማብረድ ጸጋ ሊኖረው ይገባል፡፡ ምድያማውያንን እንደሚዋጋው ዓይነት ውጊያ ከኤፍሬም ልጆች ጋር መዋጋት አይችልም፡፡ ሁለቱ በጣም የተለያዩ ውጊያዎች ናቸው፡፡ ምድያምን እንደ እባብ ብልህ ሆነን በቆራጥነት እንዋጋለን ኤፍሬምን ግን እንደ ርግብ የዋህ ሆነን በፍቅርና

በትህትና እንዋጋለን፤ የክርስትና ምስጢሩ ሁለቱንም ሚዛናዊ በሆነ መንገድ አስማምቶ መያዝ ነው::

ከዚህ ክፍል ሌላ የምንማረው ነገር ጌድዮን ያደረገውን በሙሉ ያደረገው በእግዚአብሔር ትእዛዝና ምሪት ነበር:: ነገር ግን እንዲህም ሆኖ የሚያጉረመርሙና ለምን እኛ በነገሩ ጣልቃ አልገባንም የሚሉ ሰዎች ምንጊዜም አይታጡም:: እኛ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ምሪት ተከትለን ባደረግነው ነገር እንኳን ተቃውሞና ውጊያ መነሳቱ አይቀርም:: የዚህ ዓይነቱን ውጊያ ማሸነፍ የምንችለው ግን ዝቅ በማለትና ባልንጀራችን ከእኛ እንደሚሻል በመቁጠር ነው (ፊል2:3-4)::

በምዕ 8:22-23 ደግሞ ሕዝቡ ጌድዮንን በእኛ ላይ ካልነገስክ ይሉታል::

«የእስራኤልም ሰዎች ጌድዮንን፤ ከምድያም እጅ አድነኸናልና አንተ፣ ልጅህም፣ የልጅ ልጅህም ደግሞ ግዙን አሉት:: ጌድዮንም፤ እኔ አልገዛችሁም፣ ልጄም አይገዛችሁም፣ እግዚአብሔር ይገዛችኋል አላቸው::» ሰዎች አንዳንድ ጊዜ ለእግዚአብሔር የሚገባውን ክብር ሊሰጡን ሲፈልጉ እኛ መልሰን ያንን ክብር ለእግዚአብሔር መስጠት አለብን:: ሕዝቡ ባያስተውል ነው እንጂ ከምድያም እጅ ያዳናቸው እግዚአብሔር እንጂ ጌድዮን አልነበረም::

ምዕ 8:24-27 ላይ ጌድዮን ለራሱና ለቤቱ ወጥመድ የሆነበትን ነገር ሲያደርግ እናያለን:: ከሕዝቡ በሙሉ፤ የማረካችሁትን ወርቅ ስጡኝ ብሎ ይለምንና ያንን ወርቅ ኤፉድ አድርጎ ያሠራዋል:: ይህ አሠራር ግን የእግዚአብሔርን ሐሳብ ጠይቆ ያደረገው ሳይሆን በራሱ ፍላጎት ያደረገው ነበር:: ኤፉድ፣ ሊቀ ካህናቱ ብቻ እንዲለብሱ የታዘዘው መደረቢያ (ሰደርያ አይነት) ልብስ ነው (ዘጸአት 28 ተመልከት)::

መሳ. 8:27 «ጌድዮንም ኤፉድ አድርጎ አሰራው፣ በከተማውም በዖፍራ አኖረው እስራኤልም ሁሉ ተከትሎ አመነዘረበት (ባዕድ አምልኮ ማለት ነው) ለጌድዮንና ለቤቱም ወጥመድ ሆነ::»

መሳፍንት ምዕ. 9:-

ጌድዮን ከሞተ በኋላ፤ ከቁባቱ የወለደው አቤሜሌክ የተባለው ልጁ፣ ጌድዮን ከሚስቶቹ የወለዳቸውን 70 ልጆቹን ከትንሹ በስተቀር ሁሉንም እንደገደላቸውና በእስራኤል ላይ ለሦስት አመት እንደነገሠ የሚናገር ምዕራፍ ነው።

አቤሜሌክ ይህንን ዓመፅ በወንድሞቹ ላይ በሚያደርግበት ጊዜ ተሸሽጎ ያመለጠው ትንሹ የጌድዮን ልጅ ኢዮአታም ለአቤሜሌክና ለሴኬም ሰዎች (ከአቤሜሌክ ጋር በዓመጽ የተባበሩና ያነገሡት) አንድ ምሳሌ ይነግራቸዋል። (ከቁ. 8-15) ዛፎች በላያቸው ንጉሥ ሊያነግሡ ፈልገው፣ «ወይራውን በላያችን ንገሥ አሉት፤ ወይራውም እግዚአብሔርና ሰዎች በእኔ የሚከበሩበትን ቅባቴን ትቼ በዛፎች ላይ እንድሰፍፍ ልሂድ?» አላቸው። በለስንም መጥተህ «በላያችን ንገሥ» አሉት በለሱ ግን «ጣፋጭነቴንና መልካሙን ፍሬዬን ትቼ በዛፎች ላይ እንድሰፍፍ ልሂድ?» አላቸው። ቀጥሎም ወይንን «በላያችን ንገሥ» አሉት። ወይኑም «እግዚአብሔርንና ሰውን ደስ የሚያሰኘውን የወይን ጠጄን ትቼ በዛፎች ላይ እንድሰፍፍ ልሂድ?» አላቸው። ዛፎችም ሁሉ እሾህን መጥተህ «በላያችን ንገሥ» አሉት። እሾሁም ዛፎችን በእውነት እኔን በእናንተ ላይ ታነግሡኝ እንደሆነ ኑ! ከጥላዬ በታች ተጠጉ እንዲሁም ባይሆን እሳት ከእሾህ ይውጣ የሊባኖስንም ዝግባ ያቃጥል አላቸው።» ኢዮአታም ይህንን ምሳሌ የተናገረው በዓመጽ ላይ የተመሠረተ ሥልጣን ምን እንደሚመስል ለማሳየት ነው።

ከዚህ ምሳሌ የምንማረው <u>በአገልግሎትና</u> <u>በአምባገነንነት</u> መካከል ያለውን ልዩነት ነው። ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የተጠራነው እግዚአብሔር በሰጠን ጸጋ፣ ፍሬና ቅባት በትሕትና እንድናገለግል እንጂ በሌሎች ላይ እንድንሰለጥን አይደለም። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ እንዲህ አላቸው፤ «ደግሞም ማናቸው ታላቅ ሆኖ እንዲቆጠር በመካከላቸው ክርክር ሆነ እንዲህም አላቸው:- የአሕዛብ ነገሥታት ይገዙአቸዋል፤... እናንተ ግን እንዲህ አትሁኑ፤ ነገር ግን ከእናንተ ታላቅ የሆነ በመካከላችሁ እንደ ታናሽ፣ የሚገዛም፣ እንደሚያገለግል ይሁን በማዕድ የተቀመጠ ወይስ የሚያገለግል ማናቸው ታላቅ ነው? የተቀመጠው

አይደለምን? እኔ ግን በመካከላችሁ እንደሚያገለግል ነኝ» (ሉቃስ 22:24-27)።

እግዚአብሔር በሰጠን ጸጋና ቅባት ዝቅ ብለን ማገልገሉን ትተን በሌሎች ላይ ለመሰልጠን በሥልጣን ጥማት ከተወሰድን ጸጋችንንና ቅባታችንን አጥተን እንደ እሾህ እንሆናለን። እሾህ፣ አዳምና ሔዋን በኃጢአት ከወደቁ በኋላ በምድር ላይ እንደ እርግማን የመጣ ነገር ነው።

ዘፍ. 3፡17-18 «አዳምንም አለው:- ምድር ከአንተ የተነሳ የተረገመች ትሁን፤... እሾህንና አሜከላን ታበቅልብሃለች።» እሾህ ምንም ፍሬ የለውም፣ ቅባት የለውም፣ የሚቀርቡትን የሚወጋ፣ ተቃጥሎ የሚያቃጥል ነው።

ኢዮአታም፤ ይህንን ምሳሌ አስታኮ አቤሜሌክንና የሴኬምን ሰዎች ይረግማል እርግማኑም በአቤሜሌክና በሴኬም ሰዎች ይደርስባቸዋል። «እንዲህ ባይሆን ግን ከአቤሜሌክ እሳት ይውጣ የሴኬምን ሰዎች ይብላ፤ ከሴኬምም ሰዎች ከቤትሚሎም እሳት ይውጣ አቤሜሌክንም ይብላ» (ቁ 20)። «... የይሩበኣልም ልጅ የኢዮታም እርግማን ደረሰባቸው» (ቁ 57)።

መሳፍንት ምዕ. 10:- የእስራኤል ልጆች እንደገና በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ሥራ ሲሠሩና በጠላት ሲጠቁ እናነባለን። ቁ 8 «በዚያም ዓመት የእስራኤልን ልጆች ስቃይ አበዙባቸው...» ከስቃያቸውም ብዛት የተነሳ ወደ እግዚአብሔር በንስሐ ተመልሰው፤ «ሌሎችንም አማልክት ከመካከላቸው አስወገዱ እግዚአብሔርንም አመለኩ ነፍሱም ስለእስራኤል ጉስቁልና አዘነች» (ቁ 16)።

መሳፍንት ምዕ 11:- ያስጨንቃቸው በነበረው በአሞን ንጉሥ ላይ እግዚአብሔር ዮፍታሄን አስነስቶ ሲያድናቸው እናያለን። (አሞናውያን የሎጥ ዘሮች ናቸው (ዘፍ 19:36-38)።

ዮፍታሄ የታወቀበት አንድ ትልቅ ነገር አለ፤ እርሱም በአሞን ላይ ከመውጣቱ በፊት የተሳለው ስለት ነበረ፤

ቁ 30-31 «ዮፍታሄም በእውነት የአሞንን ልጆች በእጄ አሳልፈህ ብትሰጠኝ ከአሞን ልጆች ዘንድ በደህና በተመለስሁ ጊዜ ሊገናኘኝ ከቤቴ ደጅ የሚወጣው ማንኛውም ለእግዚአብሔር ይሆናል ለሚቃጠልም መስዋዕት አቀርበዋለሁ ብሎ ለእግዚአብሔር ተሳለ።»

ቁ 34 «ዮፍታሄም ወደ ቤቱ ወደ ምጽጳ መጣ፤ እነሆም ልጁ ከበሮ ይዛ እየዘፈነች ልትገናኘው ወጣች ለእርሱም አንዲት ብቻ ነበረች፤ ከእርስዋም በቀር ወንድ ወይም ሴት ሌላ ልጅ አልነበረውም።»

ቁ 35-36 «እርስዋንም ባየ ጊዜ ልብሱን ቀዶ:- አወይ ልጄ ሆይ! ወደ እግዚአብሔር አፌን ከፍቻለሁና፣ ከዚያውም እመለስ ዘንድ አልችልምና በጣም አዋረድሽኝ አስጨነቅሽኝ አላት። እርስዋም አባቴ ሆይ፣ አፍህን ለእግዚአብሔር ከከፈትክ፣ እግዚአብሔር በጠላቶችህ በአሞን ልጆች ላይ ተበቅሎልሃልና በአፍህ እንደተናገርህ አድርግብኝ አለቸው።»

ቁ 39 «እንደተሳለውም ስእለት አደረገባት»።

ዮፍታሄ ምን ያህል በቃሉ የፀና ሰው እንደነበረ ያሳያል። የእርሱን ብቻ ሳይሆን የልጁንም ቆራጥነት እናያለን። ልክ፣ ይስሐቅ፤ አባቱ አብርሃም ለእግዚአብሔር ሊሰዋው ሲል በመሰዊያው ላይ ተጋድሞ አንገቱን ለካራ እንደሰጠ ይህችም ልጅ እንዲሁ ራስዋን ለእግዚአብሔር መስዋዕት አድርጋ ሰጠች።

የእግዚአብሔር አንድያ ልጅ ሆኖ ሳለ ራሱን ለኃጢአታችን ሲል መሥዋዕት ያደረገውን ኢየሱስ ክርስቶስንም የሚያመለክት ታሪክ ነው።

## የኤፍሬም ሰዎችና ዮፍታሔ፤ (መሳፍንት ምዕ 12)

የኤፍሬም ልጆች በምዕ 8 ላይ ከጌድዮን ጋር እንደተጣሉት በዚህ ምዕራፍ ደግሞ ከዮፍታሔ ጋር ይጣላሉ። ቁ 1 «የኤፍሬም ሰዎች ተሰበሰቡ ወደ ጻፎንም ተሻግረው ዮፍታሔን ከአሞን ልጆች ጋር ለመዋጋት ስታልፍ ከአንተ ጋር እንድንሄድ ስለምን አልጠራኸንም? ቤትህን በአንተ ላይ በእሳት እናቃጥለዋለን አሉት።»

መቼም የሰው ማንነት የተለያየ ነውና ዮፍታሔ እንደ ጌድዮን በማባበል ሳይሆን በሰይፍ ይመልስላቸዋል፡፡ «በአፍ ይጠፉ በለፈለፉ» እንደሚባለው የኤፍሬም ልጆች እንደለመዱት አፍ እላፊ ሲናገሩ እጅ እላፊ ሲያስከትልባቸው እናያለን፡፡

ቁ 6 «... በዚያም ጊዜ ከኤፍሬም አርባ ሁለት ሺህ ሰዎች ወደቁ፡፡»

## የሳምሶን ታሪክ (መሳፍንት 13-16)

### ምዕ 13:- ስለ ሳምሶን መወለድ ለወላጆቹ የተሰጠ መመሪያ

በዚህ ምዕራፍ የምናየው ሳምሶን ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ ለእግዚአብሔር የተለየ ናዝራዊ እንደሚሆን በመልአክ ለእናቱና ለአባቱ እንደተነገረ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በእንደዚህ ዓይነት ትንቢት የተወለደ ሌላ ሰው መጥምቁ ዮሐንስ ነው (ሉቃ. 15)፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ አወላለድ ከዚህ በጣም ከፍ ያለና የተለየ ስለሆነ ከዚህ ጋር ልናወዳድረው አንችልም፡፡ በዚህ ምዕራፍ ሌላ የምናየው ነገር ቢኖር፤ በመጀመሪያ መልአኩ የተገለጠላት ለሚስትየዋ ቢሆንም ሁለቱንም የሚመለከት አደራ ስለነበረ ባልየው መልዕክቱ ለእርሱም እንዲመጣለት አግዚአብሔርን ይለምናል፡፡ እግዚአብሔርም የማኑሄን (የባልየውን) ጸሎት ሰምቶ መልአኩን ለሁለተኛ ጊዜ ሲልከው እናያለን፡፡ ባልና ሚስት ሁልጊዜ በተለይ ከእግዚአብሔር የሆነ ነገር ሲሆን ሁለቱም ከእግዚአብሔር ሰምተው በአንድነት እርምጃ መውሰድ አለባቸው፡፡

መሳፍንት ምዕ፡ 13-25 ሳምሶን በእግዚአብሔር መንፈስ እየተነቃቃ እንዳደገ እናነባለን፡፡ «የእግዚአብሔር መንፈስ በጾርአና በኤሽታዖል መካከል ባለው በዳን ሰፈር ውስጥ ሊያነቃቃው ጀመረ» የእግዚአብሔር መንፈስ በድብቅ በጓዳችን ሳያነቃቃን በገሃድ በሰዎች ፊት የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት አንችልም፡፡

### መሳፍንት ምዕ፡14:- የሳምሶን የመጀመሪያው ጋብቻና ውጊያ፤

ሳምሶን ከፍልስጥኤማውያን መካከል አንዲት ሴት አይቶ እናቱንና አባቱን አጋቡኝ ይላቸዋል፡፡ ነገሩ ከእግዚአብሔር ስለነበረ

አባቱና እናቱ መጀመሪያ በነገሩ ባይስማሙም (ባይገባቸውም) በመጨረሻ በመስማማት ሊያጋቡት አብረው ይሄዳሉ፡፡ በመንገድ ላይ በእግዚአብሔር መንፈስ ኃይል አንድ የአንበሳ ደቦል በእጁ እንደ ጠቦት ቆራርጦ ይገድላል፡፡ ከጥቂት ቀን በኋላ ይህንን ግዳዩን ለማየት ወዳለበት ቦታ በመሄድ በሬሳው ውስጥ ንብ ሰፍሮበት ያያል ከሬሳውም ውስጥ ማሩን በመውሰድ እየበላ ይሄዳል፡፡

ከዚህ ክፍል አንድ ሳምሶን የተላለፈውን ነገር ማየት እንችላለን፡፡ ናዝራዊ የሆነ ሰው ወደ ሬሳ መቅረብ እንደማይገባው የእግዚአብሔር ቃል በዘኁ 6:6-8 ይናገራል፡፡ እንኳን የእንስሳ ሬሳ ይቅርና በአባቱ፣ በእናቱ፣ ወይም በወንድሙና በእህቱ ሬሳ እንኳን መርከስ እንደሌለበት ይናገራል፤ የናዝራዊነትን ሥነ ሥርዓት በሙሉ በዘኁ 6 ላይ እናገኛለን፡፡ ሴቲቱን ካገባ በኋላ ለፍልስጥኤማውያን እንቆቅልሽ ይሰጣቸዋል፤ በእንቆቅልሹም «ከበላተኛው ውስጥ መብል ወጣ ከብርቱም ውስጥ ጥፍጥ ወጣ» አላቸው፡፡ ከሦስት ቀንም በኋላ መመለስ ሲያቅታቸው ሚስቱን በመደለል ሚስጥሩን በሚስቱ በኩል አግኝተው ይነግሩታል፡፡ ይህ ደግሞ ሌላው የሳምሶን ትልቁ ድካም ነበረ፡፡ በመጨረሻም መውደቂያ የሆነበት ይህ ድካሙ፤ ማለትም፣ ምስጢሩን በጠላት ጆሮ መናገሩ ነበረ፡፡ እግዚአብሔር ግን በዚህ በድካሙም ቢሆን ጠላቶቹን እንዲያጠቃ ሲረዳው እናያለን፡፡

መሳፍንት ምዕ:15 የራሱ ወገኖች የሆኑት የይሁዳ ሰዎች፣ ለጠላት አሳልፈው ቢሰጡትም የእግዚአብሔር መንፈስ ከእርሱ ጋር እንደ ነበረ ይገልጻል፡፡

ፊት ለፊት ከሚመጣብን የጠላት ውጊያ ይልቅ የወገኖች ተቃውሞና አለመረዳት የበለጠ አስቸጋሪ ነው፡፡ ወገኖቹ እግዚአብሔር በእርሱ በኩል መዳንን እንደሚሰጣቸው አላስተዋሉም ነበር፡፡ ነገር ግን እንዲህ ይሉታል፤ «ገዦቻችን ፍልስጥኤማውያን እንደሆኑ አታውቅምን? ያደረግህብን ይህ ምንድን ነው?» (ቁ. 11)፡፡ «አስረን በፍልስጥኤማውያን እጅ አሳልፈን ልንሰጥህ መጥተናል አሉት፤ ሳምሶንም እናንተ እንዳትገድሉኝ ማሉልኝ አላቸው» (ቁ:12)፡፡ ሳምሶን የበለጠ የፈራው ወገኖቹን እንጂ ጠላቶቹን አልነበረም፡፡ እነርሱም፤ አስረን በእጃቸው አሳልፈን እንሰጥሃለን፣ አንገድልህም ብለው ተናገሩት፡፡ የእግዚአብሔር ቃል በሐዋ 7:25 ስለ ሙሴ ሲናገር፤ «ወንድሞቹም እግዚአብሔር በእጁ መዳንን

እንዲሰጣቸው የሚያስተውሉ ይመስለው ነበር፤ እነርሱ ግን አላስተዋሉም» ይላል። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስም በዮሐ 1:11 «ወደ ገዛ ወገኖቹ መጣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም» ይላል።

የገዛ ወገኖቹም ሳምሶንን አሳልፈው ከሰጡት በኋላ የእግዚአብሔር መንፈስ በላዩ ይወርድበትና እስራቱ ሁሉ ከእጁ ይወድቃል። አንዳንድ ጊዜ ከገዛ ወገኖቻችን የሚመጣብንን ጥቃትና እስራት መቀበል አለብን ማለት ነው። የእግዚአብሔር መንፈስ መጥቶ እስራታችንን ሁሉ እስኪያስወግድልን መታገስ ይኖርብናል። ምክንያቱም ጠላቶቻችንን እንደምንዋጋ ወገኖቻችንን እንድንዋጋ አልተፈቀደልንም። የእግዚአብሔር ቃል «ብትበደሉ አይሻልምን? እናንተ ግን ትበድላላችሁ፤ ያውም ወንድሞቻችሁን» (1ቆሮ. 6÷8) በማለት የሚያስጠነቅቀን ለዚህ ነው።

የእግዚአብሔር መንፈስ ወርዶ እስራቱ ከተፈታ በኋላ በአህያ መንጋጋ አንድ ሺህ ሰው ይገድላል። ሳምሶንም «በአህያ መንጋጋ ክምር በክምር ላይ አድርጌያቸዋለሁ በአህያ መንጋጋ አንድ ሺ ሰው ገድያለሁ» አለ (ቁ:16)። ሳምሶን እግዚአብሔር በሰጠው ድል እግዚአብሔርን ሲያመሰግን አናይም፤ በራሱ ኃይል ያደረገው ይመስል ራሱን ሲያሞግስ ነው የምናየው። ይህንን ካደረገ በኋላ በጣም ስለተጠማ የሳምሶንን ጸሎት ለመጀመሪያ ጊዜ እንሰማለን። «አንተ ይህችን ታላቅ ማዳን በባሪያህ እጅ ሰጥተሃል አሁንም በጥም እሞታለሁ ባልተገረዙትም እጅ እወድቃለሁ ብሎ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ።» የመጀመሪያው ጸሎቱ እንኳን ከራሱ የሥጋ ጥማት ጋር የተያያዘ እንጂ ከእግዚአብሔር ዓላማ ጋር የተያያዘ አልነበረም። በመጨረሻ ላይም በምዕራፍ 16:28 ላይ «ስለ ሁለቱ ዓይኖቼ ፍልስጥኤማውያንን አሁን እንድበቀል እግዚአብሔር አምላክ ሆይ እባክህ አስበኝ፤ አምላክ ሆይ ይህን አንድ ጊዜ ብቻ እባክህ አበርታኝ ብሎ እግዚአብሔርን ጠራ» በማለት የጸለየው ስለ ሁለቱ ዓይኖቹ ለመበቀል እንጂ እግዚአብሔር ስለ ህይወቱ ያለው ጥሪና ዓላማ ምን እንደሆነ ገብቶት እንዳልነበረ እናያለን። በአጠቃላይ ከእግዚአብሔር ጋር ቅርብ የሆነ የግል ግንኙነት አልነበረውም። የእግዚአብሔርን ኃይል እንጂ የእግዚአብሔርን ልብና ሐሳብ አልተረዳም ነበረ።

መሳፍንት፡ 16:- የሳምሶን የመጨረሻው ውድቀትና ድል፤

ደሊላ የምትባልን አንዲት ፍልስጥኤማዊት ሴት ወድዶ ታላቅ ኃይሉ ያለበትን ምስጢር ከንዝነዘዋ የተነሣ እንደነገራትና እንዳዋራችው እናያለን፡፡ ይህ ክፍል የሳምሶንን አሳዛኝ አወዳደቅ ያሳየናል፡፡ የሳምሶን ችግር ከጠላት ጋር (ከእሳት ጋር) ጨዋታ መጫወቱ ነበር፡፡ አንድ ህፃን ልጅ ከእሳት ጋር ለመጫወት ቢል እንደሚቃጠል ሁሉ ሳምሶንም እንዲሁ ከኃጢአት ጋር ሲጫወትና ሲቃጠል እናያለን፡፡

በመጀመሪያ፤ ደሊላ እንዲህ ብላ ትጠይቀዋለች፡፡ «ታላቅ ኃይልህ ምን እንደሆነ <u>እንድትዋረድስ</u> የምትታሰርበት ምን እንደሆነ እባክህ ንገረኝ፡፡» ቁ፡ 6 እንደዚህ ግልጽ የሆነ የጠላት ወጥመድ ውስጥ ሆኖ፣ <u>ጠላት የመጣበት በሚወደው ነገር ነበርና</u> ሊያስተውል አልቻለም፡፡

ሳምሶንም «በሰባት ባልደረቀ በእርጥብ ጠፍር ቢያስሩኝ እደክማለሁ እንደሌላም ሰው እሆናለሁ» አላት፡፡ እርሷም ካሰረችው በኋላ በጓዳዋ ውስጥ ፍልስጥኤማውያንን ደብቃ «ሳምሶን ሆይ ፍልስጥኤማውያን መጡብህ» አለችው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስም፤ በዚህም ሁኔታ ውስጥ ሆኖ እንኳን ከእርሱ ጋር ስለነበረ የታሰረበትን ጠፍር በጣጠሰው፡፡

ከዚህ ታሪክ የምንማረው ትምህርት፤ የእግዚአብሔር መንፈስ አንዳንድ ነገሮችን በህይወታችን ስለሚሰራ (ኃይሉንና ጸጋውን ስለገለጠ) <u>እኛ ያለንበትን ሁኔታ ማጽደቁ አይደለም</u>፡፡ አንደንድ ጊዜ ከምሕረቱና ከቸርነቱ የተነሳ ብቻ የሚሰራበት ጊዜ አለ፡፡ እግዚአብሔር በስጦታውና በመጥራቱ ስለማይጸጸት ስለ ስጦታው ሲል ይሰራል፤ ይህንን ግን፣ ያለንበትን ሁኔታ ማጽደቁ እንደሆነ አድርገን መውሰድ የለብንም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ስለተገልጋዮቹ ሲል ብቻ ይሠራል፡፡

ሌላ ከዚህ ክፍል የምናየው፤ በጓዳ ውስጥ ጠላቶች አድፍጠው እየተጠባበቁት እርሱ ግን ሳያስተውል ከጠላት መልዕክተኛ (ደሊላ)

ጋር ድብብቆሽ ይጫወት ነበር። እኛስ በጊዳችን አድፍጦ የሚጠባበቀን ጠላት ይኖር ይሆን? የሳምሶን ዋናው ስህተት የራሱን ስፍራ ትቶ በጠላት ካምፕ ውስጥ ሆኖ ጠላትን መዋጋት ፈለገ። «የሚቀጠቅጥ በአንተ ላይ ወጥቶአል ምሽግን ጠብቅ መንገድንም ሰልል ወገብህን አጽና ኃይልህንም እጅግ አበርታ» ናሆም 2:1 ይለናል። በተጨማሪም፤ በዘፍ 4:7 ላይ እግዚአብሔር ለቃየን የሰጠ ውን ምክር እናስብ፤ «ኃጢአት በደጅ ታደባለች ፈቃድዋም ወዳንተ ነው አንተ ግን በእርስዋ ንገስባት።» ሳምሶን ግን ይህንን ስላላስተዋለ ኃጢአት በእርሱ ላይ ሲነግስበት እናያለን።

ቀጥሎም ሥራ ባልተሰራበት በአዲስ ገመድ ቢያስሩኝ እደክማለሁ ይላታል። ከዚያም የራሴን ጠጉር ሰባቱን ጉንጉን ከድር ጋር ብትጎነጉኚው በችካልም ብትቸክይው እደክማለሁ ይላታል። ከዚህ ሁሉ የምናየው ምስጢሩን ወደ መንገር እያዘገመ እንደሆነ ነው። እግዚአብሔር በውስጡ ያስቀመጠውን የከበረ ነገር በጠላት ፊት ሲጥል እናያለን። «ዕንቁአችሁን በእርዮች ፊት አትጣሉ» ብሎ የእግዚአብሔር ቃል የሚያስጠነቅቀን ለዚህ ነው። «በእግራቸው እንዳይረግጡት ተመልሰውም <u>እንዳይነክሱአችሁ</u> የተቀደሰውን ለውሾች አትስጡ» (ማቴ 7: 6)።

በመጨረሻም በጣም ስለነዘነዘችው «ነፍሱ እስከሞት ድረስ ተጨነቀች» (ቁ 16)። ዓለምንም እግዚአብሔርንም ለማስደሰት ስንሞክር ነፍሳችን በውጥረት ውስጥ ትሆናለች።

«ማንም ዓለምን ቢወድ የአባት ፍቅር በእርሱ ውስጥ የለም» (1ዮሐ 2:16)።

ሳምሶንም ነፍሱ ተጨንቃለችና እውነተኛውን ምስጢር ገለጠላት፤ ደሊላም የልቡን ሁሉ እንደነገራት ስለተረዳች ፍልስጥኤማውያንን ጠርታ በጉልበትዋ ላይ አስተኝታ ጸጉሩን ሁሉ አስላጨችው፣ ልታዋርደውም ጀመረች፣ ኃይሉም ከርሱ ሄደ» (ቁ 19)። ሳምሶንም «ከእንቅልፉ ነቅቶ እወጣለሁ እንደወትሮውም ጊዜ አደርጋለሁ አለ <u>ነገር ግን እግዚአብሔር ከእርሱ እንደተለየው አላወቀም»</u> (ቁ 20)። ሳምሶን የጠላቱን ጉልበት ተንተርሶና

ተደላድሎ በመተኛት ጺጋው ሁሉ ሲገፈፍ አላወቀም፡፡ አሁንም ጨዋታ ላይ ያለ መስሎታል፡፡

«ፍልስጥኤማውያንም ይዘው <u>ዓይኖቹን አወጡት</u> ወደ ጋዛም አምጥተው <u>በናስ ሰንሰለት አሰሩት በግዞትም ሆኖ እያለ ይፈጭ ነበር</u>» (ቁ 21)፡፡ እግዚአብሔር ለወገኖቹ መዳን ለጠላቶቹ ደግሞ ውርደትን እንዲያመጣ የቀባው ሰው እራሱ በጠላቶቹ ሲዋረድ እና መጫወቻ ሲሆን በጣም ያሳዝናል፡፡ ሳምሶንንም ከግዞት ቤት ጠሩት በፊታቸውም <u>ተጫወተ ተዘባበቱበትም</u>» (ቁ 25)፡፡

ነገር ግን እግዚአብሔር ቸርና መሐሪ ስለሆነ፤ «የራሱም ጠጉር ከላጩት በኋላ ያድግ ጀመር» (ቁ 22)፡፡ ጸጉሩ የጺጋ ምሳሌ ነው፡፡ የተወሰደበት ጺጋ ቀስ በቀስ ሲመለስለት እናያለን፡፡ በመጨረሻም እግዚአብሔርን «እባክህ አስበኝ አምላክ ሆይ ይህን አንድ ጊዜ ብቻ አበርታኝ» ብሎ ይለምናል (ቁ 28)፡፡ እግዚአብሔር ጸሎቱን እንደሰማለት በማመን «ከፍልስጥኤማውያን ጋር ልሙት አለ፤ ተጎንብሶም ምሰሶቹን በሙሉ ኃይሉ ገፋ፤ ቤቱም በውስጡ በነበሩት ላይ ወደቀ፤ በሞቱም የገደላቸው ሙታን በሕይወት ሳለ ከገደላቸው በዙ፡፡»

ይህ የመጨረሻው እምነትና ሰማዕትነት ሳይሆን አይቀርም ሳምሶን በዕብራውያን ምዕራፍ 11 ላይ ከእምነት ጀግኖች ጋር አብሮ እንዲጻፍ ያደረገው (ዕብ 11:32)፡፡

## III. አንዳንድ ታሪካዊ ድርጊቶች መሳፍንት (ምዕ 17-21)

በእነዚህ አምስት ምዕራፎች ሁለት ዐቢይ ታሪኮችን እናነባለን፡፡

ሀ) ሚካ የሚባል ሰው ታሪክ (ምዕ 17-18)
ለ) በአንድ ሌዋዊና በቁባቱ ላይ የደረሰ ታሪክ (ምዕ 19-21)

ሀ. የሚካ ታሪክ

በምዕ 17፤ ሚካ የሚባለው ሰው ከእናቱ አንድ ሺ አንድ መቶ ብር ሰርቆ፤ እናቱ ማን እንደሰረቀ ሳታውቅ የሰረቀውን ሰው ትረግማለች፡፡ ሚካም የእናቱን እርግማን ሲሰማ ፈርቶ የሰረቀው ሰው እርሱ እንደሆነ ይነግራታል፡፡ እርሷም ልጄ ሆይ እግዚአብሔር ይባርክህ ትለዋለች (ቁ 2)፡፡

ከዚህ ክፍል የምንማረው፤ በበደላችንና በኃጢአታችን እርግማን በራሳችን ላይ ሲያንዣብብ ኃጢአታችንን አውቀንና ተጸጽተን ንሥሐ ብንገባ፣ እግዚአብሔር እርግማኑን ወደ በረከት እንደሚለውጠው ነው፡፡ እርግማን በተነገረበት አንደበት ሲባረክ እናያለን፡፡ በተለይ (ለልጆች፤ ትላልቅ ልጆችም ልንሆን እንችላለን) ትልቅ ትምህርት አለው፡፡ በአንዳንድ ሁኔታዎች ከወላጆቻችን እርግማን ቢሰነዘርብን (በተለይ በእኛ ኃጢአትና መተላለፍ) ያንን እርግማን ወደ በረከት መለወጥ እንደምንችል ያሳየናል፡፡

እናቱ «እግዚአብሔር ይባርክህ» አለችው፡፡ በኋላ እንደውም ያንን ገንዘብ ስለ አንተ ለእግዚአብሔር እቀድሰዋለሁ ብላ ቀልጦ የተሰራ ምስልና የተቀረጸ ምስል አሰራችበት፡፡ ይህ አደራረግ በግል እግዚአብሔር የሰጣቸውን ከአስርቱ ትእዛዛት ውስጥ ሁለተኛውን ትእዛዝ የሚተላለፍ ቢሆንም በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔርን ህግ የሚያስተምራቸውና የሚመራቸው ሰው ስላልነበረ ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር (ቁ 6 )፡፡

ምስል ማሰራት የእግዚአብሔርን ትእዛዝ መተላለፍ ቢሆንም መልካም ስለመሰላት «ለእግዚአብሔር እቀድሰዋለሁ» ብላ ነበረ ያደረገችው፡፡ ልጅዋ ሚካም በተጨማሪ የአምላክ ቤት አድርጎ እነዚህን ምስሎች በማስቀመጥ፣ አንደኛውን ልጁን ካህን በማድረግ፣ የራሱን የአምልኮ ሥርዓት ሲያቋቁም እናያለን፡፡ በአጠቃላይ ከእግዚአብሔር ቃል ከአስርቱ ትእዛዛት አንፃር ስናየው ጣኦት አምልኮ ቢሆንም፤ እግዚአብሔር ግን ያለማወቅን ወራት አሳልፎ የሚያይ አምላክ ስለሆነ በስህተት ያደረጉትን ሳይሆን የልባቸውን ፍላጎት አሻግሮ ያየ ይመስላል፡፡ ከቁ 7-13 ስናነብ አንድ ከካህናት ወገን የሆነ ሌዋዊ በአጋጣሚ (ምናልባትም በእግዚአብሔር እቅድ ሳይሆን አይቀርም) መጥቶ ካህን ሲሆንለት እናያለን ይህ ከሆነለት

በኋላ ሚካ እንዲህ ይላል፤ «ሌዋዊ ካህን ስለሆነልኝ እግዚአብሔር መልካም እንዲሠራልኝ አሁን አውቃለሁኝ (ቁ 13)::»

መሳፍንት ምዕ 18:- የዳን ነገዶች ሌሳ የምትባልን ከተማ ወግተው እንደወረሱና የሚካን ጣኦቶችና ሌዋዊ ካህን እንደወሰዱበት እናያለን::

የሚሰጥ አምላክ ለመውሰድም መብት ስላለው ያ ሌዋዊ ካህን ከሚካ ሲወሰድበት እናያለን:: የዳን ሰዎች ሌዋዊውን እንዲህ ይሉታል፤ «ለአንድ ሰው ቤት ካህን መሆን ወይስ ከእስራኤል ዘንድ ለነገድና ለወገን ካህን መሆን ይሻልሃል?» (ቁ 19):: ካህኑም በልቡ ደስ አለው ኤፉዱንም ተራፊሙንም የተቀረጸውንም ምስል ወሰደ በሕዝቡም መካከል ሄደ::

ከአሥርቱ ቃላት ሁለተኛውን ትእዛዝ፤ «በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው ከምድርም በታች በውሃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ» (ዘጸ. 20:4)» የሚለውን፤ ሚካ ብቻ ሳይሆን ሌዋዊውም የዘነጋ ይመስላል:: ሚካም ከእርሱ እንደበረቱ ባየ ጊዜ ተመልሶ ወደ ቤቱ ሄደ (ቁ 26)::

የዳን ልጆች ወግተው ስለወሰዱአት ከተማ በቁ 28 ላይ እንዲህ ይላል፤ «ከተማይቱ ከሲዶና ራቅ ያለች ነበረችና እነርሱም ከሌሎች ሰዎች ተለይተው ብቻቸውን ይኖሩ ነበርና የሚታደግ አልነበራቸውም» ይህ አባባል ለክርስትና ህይወታችን ትልቅ ትምህርት አለው:: ከሌሎች ወገኖቻችን ፈንገጥ ብለን የምንኖር ከሆነ ለጠላት ራሳችንን ማጋለጥ ይሆንብናል:: ማንም አያስፈልገኝም እኔ በራሴ ብቻ እቆማለሁ የሚል ሰው ራሱን ለምርኮና ለውድቀት እያመቻቸ ነው::

መሳፍንት ምዕ 19-21:- በአንድ ሌዋዊና በቁባቱ ላይ የደረሰ ታሪክና በደሉን የፈፀሙት የብንያም ወገኖች የደረሰባቸውን ቅጣት የሚያሳይ ክፍል ነው::

## ለ. የሌዋዊውና የቁባቱ ታሪክ

ምዕ 19:- ሌዋዊውና ቁባቱ፤

አንድ ሌዋዊ ቁባቱ አመንዝራበት ጥላው ወደ አባቷ ቤት ትመለሳለች። እርሱ ግን ዕርቅ ሽቶ አባቷ ቤት ድረስ በመሄድ ከመለሳት በኋላ ቀኑ መሽቶ ስለነበረ የብንያም ከተማ ወደሆነችው ጊብዓ ወደምትባል ከተማ ገብተው ማንም የሚያሳድራቸው ሰው ስላላገኙ በከተማው አደባባይ ተቀመጡ። በዚያች ከተማ በእንግድነት ተቀምጦ የነበረ የኤፍሬም አገር ሰው ከእርሻ ስራ ሲመለስ አይቶአቸው ወደቤቱ ያስገባቸውና ያስተናግዳቸዋል። በምሽትም አንዳንድ ወስላቶች መጥተው ወደቤትህ የገባውን ሰው እንድንደርስበት አውጣልን በማለት በሩን ሲደበድቡ በመጨረሻ የሌዋዊውን ቁባት አውጥተው ይሰጧቸዋል። በእርሷም ሌሊቱን ሁሉ እስኪነጋ ድረስ ሲያመነዝሩባት አድረው ይለቋትና መጥታ በኤፍሬማዊው ሰው ቤት ደጃፍ ትወድቃለች።

ሌዋዊው ጠዋት ተነስቶ «ተነሺ እንሂድ» ሲላት ሞታ ስለነበረ አልመለሰችለትም። ይህንንም አስጸያፊ ድርጊት ለእሥራኤል ሁሉ ለመንገር ወደ አገሩ ከገባ በኋላ ለአሥራ ሁለት ይቆራርጣትና ለአሥራ ሁለቱም ነገዶች ይልክላቸዋል። ይህም ወሬ የደረሳቸው ሁሉ የእስራኤል ልጆች ከግብጽ ከወጡ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እንዲህ ያለ ነገር ከቶ አልተደረገም አልታየምም እያሉ ይመካከሩና ይነጋገሩ ጀመር።

ከዚህ ምዕራፍ የምናያቸው ሁለት ነገሮች፤

1) የሌዋዊው ቁባት፣ በቁ 2 ላይ «አመነዘረችበት» የሚል ቃል ስናነብ በቁ 25 ላይ ደግሞ የብንያም ሰዎች «አመነዘሩባት» የሚል ቃል እናነባለን። ይህች ሴት የዘራችውን ያጨደች ይመስላል። ነፋስን ዘሩ አውሎ ነፋስንም አጨዱ ተብሎ እንደተጻፈው ይህች ሴት ከዘራችው ብዙ እጥፍ እንዳጨደች ነው የምናየው። ይህም ሆኖ የብንያም ሰዎች የፈጸሙት አስጸያፊ ነገር አግባብ ነው ማለት አይደለም።

2) የብንያም ሰዎች ልክ እንደ ሰዶምና ገሞራ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት አስጸያፊ ሁኔታ ላይ እንደነበሩ ነው የምናየው። እግዚአብሔር ቅን ፈራጅ ስለሆነ ሰዶምና ገሞራን ከቀጣ እነዚህንም መቅጣት አለበት ማለት ነው።

መሳፍንት ምዕ 20፡ - የእስራኤል ልጆችና የብንያም ልጆች መዋጋት፤

የእስራኤል ልጆች በሙሉ ብንያምን ለመውጋት እንደ አንድ ሰው በመውጣት፤ በመጀመሪያ፣ «እንገድላቸው ዘንድ እንዲህ ያደረጉትን ምናምንቴ ሰዎች አውጥታችሁ ስጡን» በማለት የብንያምን ሰዎች የጠየቁትን ጥያቄ የብንያም ሰዎች ስላልተቀበሉ የብንያምን ሰዎች ለመውጋት ወደ ጊብዓ ተሰበሰቡ።

የብንያም ሠልፈኞች 26,700 ሲሆኑ (ቁ. 15) የእስራኤል ሠልፈኞች ግን 400,000 ነበሩ (ቁ 17) በቁጥር ብልጫ ቢሆን የእሥራኤል ሰዎች ብንያማዊያንን በአንድ ጊዜ ማጥፋት ነበረባቸው ነገር ግን ጥሉ በሁለት ወንድማማች በሆኑ ወገኖች፣ ለዚያውም ሁለቱም የእግዚአብሔር ሕዝቦች ስለነበሩ፤ እግዚአብሔር የብንያምን ወገን የመታው፤ በመጀመሪያ፣ ሁለት ጊዜ የእስራኤል ልጆች በብንያም ልጆች ተሸንፈው ብዙ ሺህ ሰዎች ካለቀባቸው በኋላ ነበረ። ይህ ክፍል በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል ለሚነሳ ግጭትና ጦርነት ትልቅ ማስጠንቀቂያ የሚሆን ትምህርት አለው። ትምህርቱም፤ በወንድምህ ዓይን ውስጥ ያለውን ጉድፍ ከማውጣትህ በፊት በራስህ ዓይን ያለውን ምሰሶ አውጣ የሚል ነው።

ሁኔታውን በቅደም ተከተል እንመልከት፤

1) በመጀመሪያ የእስራኤል ልጆች እግዚአብሔርን፤ «የብንያምን ልጆች ለመውጋት አስቀድሞ ማን ይውጣልን?» ብለው ይጠይቃሉ (ቁ 18)። እግዚአብሔርም ይሁዳ ይቅደም ይላል።

እግዚአብሔር «ይሁዳ ይቅደም» አለ እንጂ በብንያም ላይ ድልን እሰጣችኋለሁ አላለም። የእስራኤል ልጆችም ከብንያም ጋር ገጥመው ሃያ ሁለት ሺ ሰዎች ይገደሉባቸውና በብንያም ልጆች ይሸነፋሉ። ነገሩ ግራ ገባቸው። እነርሱ ለእግዚአብሔር

ቀንተው እንዴት በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል እንደዚህ ዓይነት አስጸያፊ ነገር ይደረጋል ብለው ነበረ፣ በብንያም ላይ የወጡት። ጥያቄው ግን እነርሱ እራሳቸውስ እግዚአብሔር እንደሚፈልጋቸው ነበሩ ወይ? በሌላው መፍረድና የሌላውን ስህተት ማየት ቀላል ነው። የራሳችንን ስህተት ግን ማየት አንችልም።

2) በሁለተኛው ጊዜ «በእግዚአብሔር ፊት እስከ ማታ ድረስ አለቀሱ እግዚአብሔርንም «ከወንድሞቻችን ከብንያም ልጆች ጋር ለመዋጋት ዳግመኛ እንቀርባለን» ብለው ጠየቁ» (ቁ 23)። በዚህ ጊዜ አመለካከታቸው ትንሽ ለወጥ ያለ ነበረ። በእግዚአብሔር ፊት አለቀሱ። በመጀመሪያው ጊዜ ይህንን አላደረጉም ነበረ። የብንያምን ልጆች ወንድሞቻችን ማለት ጀመሩ። ይህ ትልቅ ለውጥ ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ ምንም ቢበድልና ቢተላለፍ አሁንም ወንድሞቻችን እንደሆኑ መዘንጋት የለብንም። በመጀመሪያው ጊዜ «የብንያምን ልጆች ለመውጋት አስቀድሞ ማን ይውጣልን» ነበር ያሉት። አሁን ግን «ከወንድሞቻችን ከብንያም ልጆች ጋር ለመዋጋት ዳግመኛ እንቀርባለን?» ብለው ጠየቁ።

በሉቃስ 15 አባካኙ ልጅ ወደ ቤቱ በተመለሰ ጊዜ ታላቅ ወንድሙ «ወንድሜ» ብሎ ሊጠራው እንዳልወደደ ሁሉ እነዚህም የብንያምን ልጆች ወንድሞቻችን ብለው ለመጥራት በመሸነፍ ውስጥ ማለፍ ነበረባቸው።

አጠያየቃቸው ሄደን እንውጋቸው እናስተምራቸው ከሚል መንፈስ ሳይሆን «ለመዋጋት ዳግመኛ እንቀርባለን?» የሚል ነበረ። እግዚአብሔርም፤ በእነርሱ ላይ ውጡ አለ። አሁንም ቢሆን ድል እሰጣችኋለሁ አላላቸውም። «በእነርሱ ላይ ውጡ»፤ ነገር ግን ገና የምትማሩት ትምህርት አለ» ማለቱ ነበር። በእነርሱ ላይ ከወጡም በኋላ እንደገና ሲሸነፉና 18,000 ሰዎች ሲሞቱባቸው እናያለን።

3) ከዚህ በኋላ ቅስማቸው ሳይሰበር አይቀርም። ምነው እግዚአብሔር ሆይ! ውጡ ብለኸን እንደዚህ ታዋርደናለህ ሳይሉ አይቀርም። «በዚያም ቀን እስከ ማታ ድረስ ጾሙ፣ በእግዚአብሔር ፊት

የሚቃጠልና የደኅንነት <u>መሥዋዕት አቀረቡ</u>» (ቁ 26)፡፡ በዚህ ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ማልቀስ ብቻ ሳይሆን፤

ሀ) እስከማታ ድረስ ጾሙ

ለ) የሚቃጠልና የደኅንነት መሥዋዕት አቀረቡ

ሐ) በቃል ኪዳኑ ታቦትና በካህኑ በፊንሐስ ፊት ቆመው እግዚአብሔርን ጠየቁ» (ቁ 27-28)፡፡

አሁን ትክክለኛው ቦታ የመጡ ይመስላል፡፡ እራሳችን ትክክለኛው፣ እግዚአብሔር የሚፈልገን ቦታ ሳንሆን ወንድሞቻችንን ማን ቀጪ አደረገን? በእግዚአብሔር ፊት በጾምና በጸሎት በምልጃ ስለነገሩ ሳንቀርብ፣ ራሳችንን በመጀመሪያ ሳንቀድስና ሳናስተካክል ማን ፈራጅ አደረገን? በወንድምህ ዓይን ያለውን ጉድፍ አታውጣ አላለንም፤ ነገር ግን በመጀመሪያ የራስህን ጣጣ ጨርስ ነው ያለን፡፡

በዚህ ጊዜ ጥያቄአቸውም ለየት ያለ ነበረ፡፡ «ከወንድሞቻችን ከብንያም ልጆች ጋር <u>ለመዋጋት ዳግመኛ እንወጣለን ወይስ እንቅር</u> ብለው ጠየቁ» (ቁ 27)፡፡

ወደ ብንያም የወጡት <u>በመሐላ</u> እንደነበረ በምዕ 22፣5 ላይ እናነባለን፡፡ በብንያም ላይ ያልወጣ ይገደል ብለው በፍርድና በድንፋታ ነበረ የወጡት፡፡ አሁን ግን እግዚአብሔር ካስተማራቸው በኋላ መሐላችንም ይቅር፤ አንተ አትውጡ ካልክ እንቀራለን የሚል መንፈስ ይዘው ነበረ ወደ እግዚአብሔር የቀረቡት፡፡ «እግዚአብሔርም ነገ በእጃችሁ እሰጣቸዋለሁና ውጡ አለ» (ቁ 28)፡፡

ለመጀመሪያ ጊዜ፤ «<u>ድልን እሰጣችኋለሁና ውጡ</u>» አላቸው፡፡ ምክንያቱም አሁን ከዓይናቸው ውስጥ ምሰሶውን ስላወጡ ወንድሞቻቸውን ለመቅጣት ይጠቀምባቸዋል፡፡

ይህም ሆኖ:- «እግዚአብሔርም ብንያምን በእስራኤል ፊት መታ» (ቁ 35) ይላል እንጂ፣ እስራኤላውያን ብንያማውያንን መቱ

**አይልም። ወንድሞቻችን ቢያጠፉም እንኳን እግዚአብሔር እንጂ እኛ እንዳንመታ መጠንቀቅ አለብን።**

**መሳፍንት ምዕ 21:- የብንያም ቅሬታ (Remnant)**

**የብንያም ሠራዊትና ሕዝቡ፣ ከብቶቻቸውም ሁሉ ከተደመሰሱ በኋላ ስድስት መቶ ወንዶች ብቻ በዋሻ ተሸሽገው ስለተረፉ ከእስራኤል አንድ ነገድ ፈጽሞ እንዳይጠፉ እስራኤላውያን ተጸጽተው፤ እንዴት ለ600ው ሰዎች ሚስቶችን እንዳዘጋጁላቸው የሚገልጽ ምዕራፍ ነው።**

**ከዚህ ምዕራፍ የምናየው፤ እግዚአብሔር ምንም ቢቆጣና ቢቀጣም ቅሬታን የሚያስቀር አምላክ እንደሆነ ነው። በእግዚአብሔር ምህረት ባይሆን ኖሮ የብንያም ዘር ፈጽሞ ተደምስሶና ጠፍቶ ነበረ።**

**«ያልጠፋነው ከእግዚአብሔር ምህረት የተነሳ ነው»**
**(ሰቆ ኤር. 3:22)**

**የሚለው ቃል ለብንያማውያን ብቻ ሳይሆን ለእያንዳንዳችን የሚሆን ቃል ነው።**

*Global Good News Literature*

*P.O.Box 451336*

*Los Angeles, CA 90045*

(C) Copyright 2013 Global Good News Literature